መግለጫ፦ (አባሪ 3) (ካለንድሩን ለመገልገል ይህን አባሪ ማንበብና መረዳት ያስፈልጋል)

1. በካለንደሩ (ቀን መቁጠሪያው) ላይ የተመለከተው ዝግጅት የተመሠረተው በአውደ ፀሐይ ላይ ነው ። አንድ ዐውደ ፀሐይ 28 ዓመት ነው ።
2. በ 7 ምድብ የተከፈለው የመባቻውን ዕለት አንድነት መሠረት በማድረግ ዘመናቱን በነዚህ ምድቦች ቋቶች አካቶ ለመያዝ ነው።
3. በየምድቡ ቋት የሚገኙት 4፣4 አህዞች አንድ ላይ መሆን የሚያገለግለው የመባቻቸው ዕለት አንድነት ለመግለጽ ነው።
4. አህዞቹ እያንዳንዱ ዘመን (ዓመተ ምሕረት) ለ 28 ሲካፈል (በ 28 ሲገደፍ) የሚገኙ ቀሪዎች ናቸው። በዚህ መሠረት ፣
   ሀ/ ቀሪው 1፣7፣12፣18 ሲሆን ምድብ 1 የዘመን መባቻቸው ዕለት ረቡዕ ነው። (አባሪ 1 ን ተመልከት፤)
   ለ/ ቀሪው 2፣13፣19፣24 ሲሆን ምድብ 2 የዘመን መባቻቸው ዕለት ሐሙስ ነው። (አባሪ 1 ን ተመልከት፤)
   ሐ/ ቀሪው 3፣8፣14፣25 ሲሆን ምድብ 3 የዘመን መባቻቸው ዕለት ዓርብ ነው። (አባሪ 1 ን ተመልከት፤)
   መ/ ቀሪው 9፣15፣20፣26 ሲሆን ምድብ 4 የዘመን መባቻቸው ዕለት ቅዳሜ ነው። (አባሪ 1 ን ተመልከት፤)
   ሠ/ ቀሪው 4፣10፣21፣27 ሲሆን ምድብ 5 የዘመን መባቻቸው ዕለት እሑድ ነው። (አባሪ 1 ን ተመልከት፤)
   ረ/ ቀሪው 5፣11፣16፣22 ሲሆን ምድብ 6 የዘመን መባቻቸው ዕለት ሰኞ ነው። (አባሪ 1 ን ተመልከት፤)
   ሰ/ ቀሪው 0፣6፣17፣23 ሲሆን ምድብ 7 የዘመን መባቻቸው ዕለት ማክሰኞ ነው። (አባሪ 1 ን ተመልከት፤)
5. መባቻቸው አንድ የሆኑት (በአንድ ዕለት የሚብቱት) የተጣምሩ አውራጎም በአባሪ 1 ሠንጠረዥ ላይ ስለተመለከቱ፣ ምንና ምን መሆናቸውን ልብ ይሏል።ያለ አጣማሪ ብቻውን (ቀንጃ) ሆኖ የቀረው መጋቢት ብቻ ነው።
6. ከምድብ 1 እስከ ምድብ 7 አራት አራት ከተጻፉት መካከል በአህዝ 7፣19፣3፣15፣27፣11 እና 23 የተጻፉት የፀሐይ ዓመታት ወይም በአባሪ 1 በ 1 ኛው አቆልቋይ በየምድቡ 3 ኛ ረድፍ የተጻፉት ዘመነ ሉቃስን ይወክላሉ። በሉቃስ ዘመኑ ስለሚያሰግር፣ ጳጉሜን 6 ይሆናል።

7 አባሪ 2 እንደተመለከተው 200 አውደ ፀሐይ ተሰልቷል። እስከ 3892 ዓ/ም ድረስ የምትፈልጉትን ዘመን

ለማስላት ሳትቸግሩ ከሚቀርበው ጋር በማነፃፀር ልዩነቱን መውሰድና ምድቡን መለየት ይቻላል።

ከዚያም ካለንደሩን መገልገል ነው።